SALZBURG GLOBAL SEMINAR

EDUCATION FOR TOMORROW'S WORLD

# የሳልዝበርግ መግለጫ ለልሳነብዙ አለም

ዛሬ እርስበርስ በተሳሰረችው አለማችን በልዩ ልዩ ቋንቋወች መናገርና በልሳናት መካከል ያሉትን ድንበሮች ተሻግሮ መግባባት መቻል እጅግ አስፈላጊ ችሎታ ሆኗል። ከአንድ በላይ ቋንቋ በከፊልም ቢሆን ማወቅ ጠቃሚ ነው። ከአንድ በላይ በሆኑ ቋንቋዎች በቂ ችሎታ መያዝ አዲሱ አለማቀፍ የመሰረተ ትምህርት መመዘኛ ሆኗል። ተጨማሪ ቋንቋዎችን የመማር እድል ለሁሉም - ለወጣቱም ለአዛውንቱም ሊዳረስ ይገባል።

ይሁን እንጅ፣ ዛሬ በልዩ ልዩ የአለማችን ክፍል የሚገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች የማንነታቸውና የጋራ ህይወታቸው ስርና መሰረት የሆኑትን ቋንቋዎቻቸውን እንዳይንከባከቡ፣ እንዳይጠቀሙና እንዳያሳድጉ ተደርገው የማይገፈፍ መብታቸውን ተቀምተዋል። ይህ ኢፍትሃዊ ጭቆና የልሳነብዙ ማህበረሰቦችንና ግለሰቦችን በሚደግፉ የቋንቋ ፖሊሲወች ሊስተካከል ይገባል።

እኛ በሳልዝበርግ አለማቀፍ ሴሚናር የቋንቋ ትምህርትና መስተጋብር በግሎባላይዜሽን ዘመን (ከታኅሣሥ 3 እስከ ታኅሣሥ 8 2010 ዓ.ም. salzburgglobal.org/go/586) በሚል ርእሰጉዳይ ተሳታፊ የሆን ለልሳነብዙነት ዋጋ የሚሰጡና የቋንቋ መብቶችን የሚያስከብሩ ፖሊሲወች እንዲወጡ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ይህ የዛልዝበርግ መግለጫ ለልሳነብዙ አለም በቁልፍ ርእሶች ላይ በ2010 ዓ.ም. በሚታተሙ ዝርዝር ሪፖርቶችና ብሎጎች እየተደገፈ ይቀርባል።

## ዛሬ በምንኖርባት አለም ውስጥ:-

- 193ቱ የተ.መ.ድ. አባላትና አብዛኞወቹ ህዝቦች ልሳነብዙ ናቸው።
- 7,097 ቋንቋወች ዛሬ በአለማችን ላይ ይነገራሉ።*
- ከነዚህ ውስጥ 2,464ቱ የመጥፋት አደጋ ላይ ናቸው።
- 23ቱ ቋንቋወች የኀለበቱና በግማሹ የአለም ህዝብ የሚነገሩ ሆነዋል።
- 40% የሚሆኑት ህዝቦች በራሳቸው ቋንቋ የመማር እድል አያገኙም።
- 617 ሚሊዮን ህጻናት እና ጎልማሶች መሰረታዊ የንባብ ክህሎት ሳያዳብሩ ይቀራሉ።
- 244 ሚሊዮን ህዝቦች ካገራቸው ውጭ የሚኖሩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 20 ሚሊዮን ያህሉ ለስደት የተዳረጉ ናቸው። ይህም ከ1992 ዓ.ም. ጋር ሲነጻጸር የ41% ብልጫ አለው። ከሃገራቸው ውጭ የሚኖሩና ለስደት የተዳረጉ ሰወች ሁሉ ባንድ ላይ ቢኖሩ ኖሮ በህዝብ ቁጥር የአለም 5ኛ ሃገር ይሆኑ ነበር።

በእውነቱ አለማችን ልሳነብዙ ናት። ሆኖም በርካታ የትምህርትና የኢኮኖሚ ስርአቶች፣ እንዲሁም የዜግነትና የማህበረሰብ አስተዳደር መርሆወች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች ላይ ቋንቋቸውንና የቋንቋ ችሎታቸውን ምክንያት በማድረግ መድሎ ያደርሱባቸዋል። በ2007 ዓ.ም. 193 ሃገሮች"ድህነትን ማጥፋት፣ ምድራችንን መጠበቅና ብልጽግናን ለሁሉም ማዳረስ" በሚል ያወጡትን የዘላቂ ልማት ግቦች እንድናሳካ ካስፈለገ ይህንን ጭቆና ማስወገድ አለብን። በጠንካራና ተገቢ የቋንቋ ፖሊሲ ላይ የተገነባ ፍትሃዊ የትምህርት ስርአት ሁሉን አቀፍ ለሆነ እድገት ዋና መሰረት ነው።

## መርሆወች

- ልሳነብዙነት በግልጽ ቋንቋን ከማስተማርና፣ የብዙ ቋንቋ ባለቤት የሆኑ ማህበረሰቦች ከሚጠቀሙባቸው መደበኛ ያልሆኑ የመግባቢያ መንገዶች የሚመነጩትን ሁሉ ያጠቃልላል።
- መድብለቋንቋ ግለሰቦች የሚጠቀሙባቸው የንብርብር ቋንቋዎች እውቀት ማለት ነው።
- ታሪካዊ፣ መልካምድራዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታወች ልዩ ልዩ አይነትና ጠቀሜታ ያላቸው ልሳነቋንቋወች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆነዋል።
- የልሳነብዙ ትምህርትና፣ መንግስትና አለማቀፍ ተቋማት ለማህበራዊ ልሳነትምህርት የሚያደርጉት ድጋፍ የእውቀትና የባህል ልውውጥንና አለማቀፍ ግኑኝነትን ያጠናክራል።

በአግባቡ የታቀዱ የቋንቋ ፖሊሲዎች ማህበራዊ ትስስርን፣ የትምህርትን ውጤታማነትና የኢኮኖሚ ልማትን ያስፋፋሉ። የተጨማሪ ቋንቋ ትምህርት መስፋፋት ህጻናት ጠንካራ የማንበብና የመጻፍ ክህሎት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል፤ ማህበረሰቦች የማንነታቸው፣ የእውቀታቸውና የእምነታቸው ምንጭ የሆኑትን ቋንቋወቻቸውን እንዲንከባከቡ ይረዳቸዋል፤ ግለሰቦችም ለመዝናናት ወይም የባህልና የኢኮኖሚ ጥቅም ለማግኘት እድል ይከፍትላቸዋል። ልሳነብዙነትን የሚያስፋፋ ፖሊሲ መከተል ለህብረብዙ ቋንቋወች ህልውና መሰረት የሆኑትን ልዩና ወሳኝ ግብአቶች ለመጠበቅ ከማስቻሉም በላይ በምድራችን አወንታዊ የሆኑ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ለውጦችን ያነሳሳል።

**ስለሆነም ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ተቋማትና መንግስታት የልሳነብዙነትን አስተሳሰብ ከልብ በመቀበል ህብረቋንቋዊነትን ማለትም የሁሉም ቋንቋወች ህልውና መጠበቅና ማደግን እንደአለማቀፍ መርህ እንዲከተሉ፤ ቋንቋን መሰረት ያደረገ መድሎ እንዲያስወግዱና፣ ልሳነብዙነትን የሚያሳድጉ ፖሊሲወችን እንዲያወጡ አበክረን እናሳስባለን።**



The *Salzburg Statement for a Multilingual World* was jointly drafted in English by Salzburg Global Fellows.
All translations have been provided through the goodwill and voluntary efforts of the Fellows and their colleagues.
Read the original here: education.salzburgglobal.org/statements

## አስተያየቶች

### ፖሊሲ አወጣጥ

ውጤታማ የቋንቋ ፖሊሲ የማህበረሰቡ አካላት የነቃ ተሳትፎና የባለሞያወች ድጋፍ ያስፈልገዋል። ምክንያታዊና ግልጽ የሆነ የቋንቋ ፖሊሲ አለ ማለት የሚቻለው:-

- ትክክለኛና ሊተገበሩ የሚችሉ ግልጽ ግቦች በውይይት ሲለዩ።
- ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በተለይም መምህራንን በየደረጃው የሚያሳትፍ የፖሊሲ ሂደት ሲኖር።
- ፖሊሲው ከቅድመ ትምህርትቤት እስከ ድህረ ትምህርትቤት የሚሰጠውን ትምህርት፣ መደበኛ ካልሆነው ትምህርትና በባህልና በህይወት ተሞክሮ ከሚገኘው እውቀት ጋር የሚያስተሳስር ሲሆን።
- ንውስ ቁጥር ያላቸው ማህበረሰቦችን የአፍመፍቻ ቋንቋ ከመጠበቅ፣ ከመማርና ከመጠቀም ጀምሮ፣ ፖሊሲው ከሁሉም የቋንቋ ሃብቶችና ፍላጎቶች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን።
- በአፍመፍቻና በሌሎች ቋንቋወች አስተምህሮት ላይ ከሚደረጉ የትምህርትና የግንዛቤ ምርምሮች ላይ ጠቃሚ ሃሳቦችን መውሰድ።
- የመገናኛ ቴክኖሎጅወችን እምቅ ችሎታ መጠቀም።
- ለተሟላ የፖሊሲ ትግበራ በቂ ግብአቶችን መመደብ።
- የፖሊሲውን አላማና አተገባበር ዘወትር መከታተልና መገምገም።

### ትምህርትና ማስተማር

ሁሉን አቀፍ የቋንቋ ፖሊሲ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ገጽታወችን ያቅፋል። የእድሜ ልክ ዘለቄታ ያለው የቋንቋ ትምህርት ህዝቦች ቋንቋቸውን ለመጠበቅና ከልሳነብዙነት ተጠቃሚ ለመሆን ያስችሏዋል። የትምህርት፣ የሞያና የስራ ፖሊሲወች የልዩልዩ ቋንቋወችን መኖር ከማድነቅ በተጨማሪ የትኛውንም አይነት ቋንቋ መማርን ማበረታታትና ዋጋ መስጠት ይገባቸዋል። ህጻናትና ጎልማሶች የቋንቋ ክህሎታቸውን  ለማሳድግ፣ ለማበልጸግና እስከ እድሜ መጨረሻቸው ድረስ አብሮአቸው እንዲቆይ ለማድረግ የተቀናጀና የማያቋርጥ ድጋፍ ሊያገኙ ይገባል።

ባህላዊ እውቀቶችንና አማራጭ የአስተሳሰብ ስርአቶችን የሚያቅፍና ቴክኖሎጅን የሚጠቀም አዲስ የትምህርት ራዕይ ያስፈልጋል። ቋንቋን በንቃት ለመማር የሚቻሉባቸው ቦታወች ከትምህርትቤትና ከከፍተኛ ተቋማት ውጭም ይገኛሉ። ጎዳናወች፣ ቤቶች፣ መንደሮች፣ ማህበራዊ መድረኮችና የስደተኞች መጠለያ ቦታወች ሁሉ ቋንቋዎችን ለመማርና አስፈላጊነታቸውን ለማድነቅ ያስችላሉ።

### የትርጉም አገልግሎቶች

በልሳነብዙ ማህበረሰብ ውስጥ የትርጉም ስራ የህዝብ አገልግሎትና የመረጃ ልውውጥ መሰረታዊ አካል ነው። ፍትሃዊ ተሳትፎን በጤና፣ በትምህርት፣በኢኮኖሚና በህግ ዘርፎች ማረጋገጥ የሚቻለዉ ነጻና ሞያዊ ብቃት ያለው የቋንቋ አተረጓጎም ስርአት ሲኖር ነው።

## የተግባር ጥሪ

ለውጥን ማራመድ የሚችሉ ባለድርሻ አካላት ሁሉ ማለትም ተመራማሪወችና አስተማሪወች፤ የማህበራት ሰራተኞች፣ ሲቪክ ማህበረሰቡና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ የባህልና የመገኛ ብዙሃን ልሳናት፤ የመንግስትና የህዝብ ባለስልጣናት፣ የንግድ ተቋማት፣ የእርዳታና የልማት ወኪሎች፣ እንዲሁም ለጋሽ አካላት:- የሚከተሉትን ለመፈጸም እንዲተባበሩ እንጠይቃለን።

- ለልሳነብዙነትና ለመድብለቋንቋ መልካም አመለካከት ያላቸው ጤናማና ተራማጅ ማህበረሰቦችን የሚደግፉ የቋንቋ ፖሊሲወችን፣ ተግባራትንና ቴክኖሎጅወችን ማውጣት።
- በመንግስታዊ ሰነዶችና ለህዝብ በሚቀርቡ መልእክቶች ውስጥ የቋንቋ መብትን፣ ብዝሃነትንና ዜግነትን በአፅንኦት መደገፍ።
- ከቋንቋና፣ ከማንበብና መጻፍ ልማድ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ መድልዎችን፣ ንቀትን፣ ጭፍን ጥላቻንና ማበላለጥን ማስወገድ።
- አናሳ ቁጥር ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ካገራቸው ውጭ የሚኖሩና ለስደት የተዳረጉ ሰወች ሁሉ ላሁኑና ለመጭው አለማችን ህልውና ከፍተኛ የሆነ የቋንቋ ሃብት እንደያዙ መቀበል።

---

**እያንዳንዳቸው ባለድርሻ አካላት በራሳቸው ልዩልዩ መንገዶች ለማህበራዊ ስልጣኔ፣ ለማህበራዊ ፍትህና ለዜጎች ተሳትፎ መረጋገጥ ልሳነብዙነትን ሊቀበሉና ሊደግፉ ይችላሉ። ሁላችንም የመጭው ትውልድ እምቅ የባህልና የእውቀት ሃብት መኖሪያ የሆኑትን ልሳነቋንቋወች እንንከባከብ።**

*You can find references for all statistics online: education.salzburgglobal.org/statements